# አያ ጅቦ በምግብ ዋስትና ሳታመካኝ ብላኝ !

በአለፈው ግንቦት ወር (May 18th 2012) እራሳቸውን የቡድን ስምንት የሚሉት ሀገራት መሪዎች በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ ስብሰባ ላይ በፕሬዘዳንት ኦባማ ጋባዥነት አራት የጥቁር አፍሪቃ ማለትም በምዕራባውያኑ ስያሜ ከሰሃራ በታች ከሚገኙት አገር መሪዎች ማለትም የጋና፣ የቤኒን፣ የታንዛኒያና የኢትዮጵያ መገኘታቸው ይታወሳል። ከሰሓራ በለይ ያሉት ለአውሮፓ ነጭ ተብዬ ክልሶች ቀረቤታ አላቸው ተብሎ ይሆናል የምግብ ዋስትናን የተመጣጠነ አመጋገብ የማያስፍልጋቸው። የጥቁር አፍሪቃውያን እጣ ፈንታና ጠቅላላ አኗናር የሚወሰነው በአውሮፓና አሜሪካውያን ላዕላይ ነጮች ነው። የቀድሞ ቅኝገዥዎችና ዘመናዊ ሞግዚቶች ለአፍሪቃ ጥቁሮች የምግብ ዋስትና ብቻም ሳይሆን ግብረ ሰዶማዊ የመሆን "ሰብአዊ መብት" እንዲከበር ታለቅ ዘመቻ ያደርጋሉ። በዚህም መሠረት በተለይ የአሜሪካና እንግሊዝ መንግሥታት ለምሳሌ በማላዊና ዩጋንዳ የፍናፍንቶች መብት ካልተከበረ ብላው ማንኛውንም ርዳታ እንደማይሰጡና የኢኮኖሚ እቀባ ማደረጋቸው ይታወቃል። በመላው አፍሪቃ ግብረሰዶማዊነትን ለማስፉፉት፣ ይልቁንም የሕዝቡን ቁጥር ለመቀነስ. በበሽታ የተበከለ ኮንዶም በነፃ በገፍ ይቀርባል። በአሜሪካን መንግሥት ርዳታ በኢትዮጵያ ለምሳሌ የቤተሰብ መምሪያ ተብሎ ሴቶችን ለማምከን በተለይ ኦሮሞና አማራው ሕዝብ ለይቶ የዘመቻው ይላማ ያደረገው እስከ ጎጥ ድረስ በመዝለቅ በሰፊው ይፈጸማል። ከዚህም ሌላ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሴቶች ወጣቶችን ለአረብ አገር ባርነት ማቅረቡን የወያኔ ቅጥረኛ በሰፊው ቀጥሎበታል። አረብ አገር የሚገኙት ኢትዮጵያውያኖች ለኢሰባዊ እንግልትና ሰቆቃ መዳረጋቸውና ብዙ ሕይወት ማለፉን የዓለም ሕዝብ ያውቀዋል።

ወደ ዋናው ቁም ነገር እንግባ። ከጉባኤው መወያያ አንዱ ዘርፍ <u>የምግብ ዋስትናና የተመጣጠነ አመጋገብ</u> ነበር። ከሁሉ በተቀዳማ ይህ የመነጋገሪያ ርእስ ማደናገሪያ ቱሪ ማንቱር ነበር። ፍጹም በዘረኝት እይታም የተሸሞነሞነ ነው። ለመሆኑ ጥቁር አፍሪቃ ብቻ ነው እንዴ ምግብ ዋስትና የሚያሻው? በዋሽንግተን ተሰብሳቢዎችና አሰባሳቢዎች እንደምታ <u>የተመጣጠነ ምግብ</u> የሚፈልጉት ጥቁር አፍሪቃኖች ብቻ ናቸው። ዳሩ ግን ሐቁ መቼ እንዲህ ነው! የእንግሊዝ፣ የአሜሪካ፣ የጀርመን፣ የጣሊያን፣ የሆላንድ ወዘተረፈ ነዋሪ ያልተመጣጠነ ምግብ በማጋበስ፣ ልክ እንደ አሳማ ዘወትር በመብላት ተድበክብከው ፈጽሞ መንቀሳቀስ እንኳ የተሳናቸው እጅግ በጣም ብዙዎች አይደሉም? በመሆኑም ክብደትን ለመቀነስ የሚደረገው ምርምር ከፍተኛ ወጪን ጠይቋል፣ ሰፊ የሥራ መስክም ፈጥሯል። ለምሳሌ በእንግሊዝ ሊቨርፑል ከተማ ሊዎ የተባለ ያምስት ዓመት ልጅ ከ70 ኪሎ በላይ ይመዝናል። ሕፃን ሊዎ በተንቀሳቃሽ ቃሬዛ ብቻ ነው ለመላወስ የሚችለው። የኒዩርክ፣ የሎንድን፣ የሽካጎ ወዘተረፈ ከተማዎች ድብክብኮች (Overweightes) ጤንነት ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጠ ነው። የክብደት ልክ አለፍ ጭመራ ያልተመጣጠነ አመጋገብ በሽታ ነው። በምዕራባውያን የመገኛ አውታሮች ዘወትር የሚለፈፈው በመጠኑ ብሉ እረጅም እድሜ ኑሩ እየተባለ ነው። የመጠንየለሽ ምግብ አመጋገብን 40% ቢቀነስ

አፍሪቃ ያውሮፓና አሜሪካ ውዳቂ ትርፍራፊና ያሮጌ የቤት ቁሳቁስና ኮምፒዩተር መጠያ ሆኖ የሚደረሰው ያካባቢ ብክለትና ቀውስ ከፍተኛ ነው። የጉባኤው መግለጭያ በግልጽ እንዳሰፈረው የምዕራባውያኑ ማለትም ያሜሪካና አውሮፓ የግል ኩባንያዎችና የንግድ ድርጅቶች እንዲሁም የሕንድ መዋእለ ንዋይ ለአፍሪካ ጥቁር አነስተኛ ገበሬዎችን የርሻ ይዞታ ማሻሻያ፣ ሴቶች በቂ ምግብ ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው እንድያመርቱ፣ እንዲገበያዩ፣ ትርፍ እንዲያገኙና ድህነት በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ውስጥ እንዲቀነስ፣ እስከ 50 ሚሊዎን ሕዝብ ከድህነት እንዲላቀቀ የተባለው አዲሱ የምግብ ዋስትናና የተመጣጠነ ምግብ ቃል ኪዳን ታውጇል።

ይሁንና የአፍሪቃን አነስተኛ ገበሬዎችን የድህንነት ኑሮ በተሰበሰቡትና ቃል በገቡት የብዙ ሀገራት ታላላቅ የምግብ አምራች ኩባንያዎችና የንግድ ድርጅቶች እንደ ካርጊል (Cargill), ዱፖንት ሞንሳንቶ፣ ክራፍት፣ ዩኒሊቨር፣ ስይንገንታ ኤጂ ወዘተረፈ በመሳሰሉት ርዳታና ትብብር ይሻሻላል ማለት ከቶውንም የማይታለም ነገር ነው። እነዚህ ኩባንያዎችና በእንዱስትሪ የበለጸጉት ሃገራት መንግሥታት ከደረሰባቸው የካፒታሊዝም ኢኮኖሚያ ቀውስ በአፍሪቃውያን ኪሳራ ከተዘፈቁበት ለመውጣት አስበው ለራሳቸው ጥቅም ማሰገኛ ሰፋፊና ለም የእርሻ መሬት፣ ለእንዱስትሪና የግብርና ምርታቸው ተጨማሪ ሰፊና አስተማማኝ ገበያና የአፍሪቃን እምቅ የማእድን የተፈጥሮ ሃብት በርካሽ ለመቀራመት ነው። ይህንንም የሚያገኙት ደግሞ በሙስና በተዘፈቁት አቀባባይ ቅጥረኛ ጉልት ኢዲሞክራሲያ መንግሥት ተብዬ አፋኝ ቡድኖች ሲሆን የአነስተኛ ገበሬዎችን ለም ይዞታና ማሳ ነጥቆ በርካሽ ለባሕር ማዶ ኩባንያዎች በማከራየት ነው። በአፍሪቃ ጀግናው የማዳጋስካር ሕዝብ ቅጥረኛውን መሬት ቸርቻሪ መንግሥት ተብዬ ባፍጢሞ ደፍቷታል። ለኮሪያ ከበርቴዎች ተሾጦ የነበረውን የርሻ መሬቱን አስመልሷል።

የኢትዮጵያን ለም ድንግል መሬት ለውጪ የግል ኩባንያዎች በርካሽ በመቸርቸር፣ አነስተኛ ገበሬዎችን የድቅል ዘርና የኬሚካል ተባይ ማጥፊያ ዘወትር ጥገኛ በማድረግ ከቶ ድህነት አይቀንስም፤ የምግብ ዋስትናም አይረጋገጥም።

ለምሳሌ የሳውድ አረቢያው አላሙዲን፣ የሕንዱ ካሩቱሪ፣ የጀርመን፣ የእንግሊዝ፣ የአሜሪካ፣ የቱርክ፣ የግብፅ፣ የቻይና፣ የኮሪያ ወዘተረፈ ኩባንያዎች የርሻ መሬት መቀራመት ለአነሰተኛ ገበሬዎች ሆነ ለኢትዮጵያ ጠቅላላ ኢኮኖሚ ምንም ጥቅም አያስገኝም። በመጀመሪያ የሚመረተው ሩዝ፣ በቆሎ፣ ሰሊጥ፣ አደንጓሬ፣ ወዘተረፈ ለሳውድ አረቢያና ለዓለም ገበያ ነው። የእርሻ መሬትና የተፈጥሮ ሃብት ቅርመታው እንዲያውም ያካባቢ ከፍተኛ ብክለትን፣ የተፈጥሮ ደን ምንጠራን፣ ያፈር ልማት ከዓመት ዓመት መራቆትንና ገበሬውን ከነፃ ሠራተኛነት ወደ ኩሊ የቀን ሠራተኝነት ያስቀይረዋል። የትልልቅ ኩባንያዎች መግባት ምክንያት የዘመናዊ እርሻ ዕውቅትና ልምድ ሽግግር ይኖራል ተብሎ የሚለፈፈው ባዶ ማወናበጃ ነው።

ኢትዮጵያ ኢትዮጵያዊ መንግሥት የላትም። ቢኖራት ኖሮ ችጋርና ድህነት በተወገዱ ነበር። ምዕራባውያን ቻይናን የችጋር አገር እያሉ ለብዙ ዓመታት ዘብተዋል። የቻይና ብሔራዊ መንግሥት ቅድሚያ ለምግብ በሚል መርህ ችጋርን ያለምንም የዓለም ባንክ፣ የአውሮፓ፣ የአሜሪካ ወዘተረፈ ርዳታ አሳግዷል።

እነዚህ ሁለቱ መንግሥታትና ተላላኪዎቻቸው በወቅቱ ሰብአዊ ርዳታ ቢያደርጉ ኖሮ የስሦት መቶ ሺህ ሕዝብ ሕይወት ሊተርፍ ይቻል እንደነበር ባለሙያዎች ገልፀዋል።

ቀጥሎም ቦብ ጊልዶፍ "ገና መሆኑን ያውቃታል?" በማለት ዘፈኑ። የምዕራብ ከተሞች በርዳታ ትርኢት ተጥለቀለቀ። ባንድ ርዳታ (Band Aid)፣ ፋሽን ርዳታ (Fashion Aid) ፣ ስፖርት ርዳታ፣ ዩኤስኤ ለአፍሪቃ (USA for Africa)፣ ወዘተረፈ የመሳሰሉት ርዳታ ሰበሰቡ።

በሐምሌ ወር እአአ 1985 ዓ.ም በተደረገው ላይቭ ርዳታ (Live Aid) ብቻ ከመቶ ሚሊዎን የአሜሪካ ብር እንደተሰበሰበና ገንዘቡም ለወያኔ ቅጥረኛ ወታደራዊ ትጥቅና ስንቅ መዋሉን የቢቢሲ ዜና አሳውቋል።

በዚያን ወቅት የነበረው የሳሂል ቀጣና ችጋር መነሻው የዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ያለመኖር ነው ተብሎ በሰፊ ተለፈፈ።

በአሜሪካን የጆርጅ ቡሽ አስተዳደር አቶ ኸርማን ኮህን አቀነባባሪነትና የእንግሊዝ መንግሥት ተባባሪነትና ይሁንታ በድኅረ ቀዝቃዛው ጦርነት ከግንቦት ወር 1983 ዓ.ም ወዲህ ወታደራዊ መንግሥት ተወግዶ ቅጥረኞች ወያኔና ሻእቢያ ገንጣይና አስገንጣይ የጎሣ ድርጅቶች ለስልጣን በቅተው አገሪቱን በፋሽስት ጣሊያን ወራሪዎች እቅድ መሠረት በጎሳ አፓርታይድ ክልል ሸንሽነው ሕዝቡን ርስ በርስ በማጋጨት የቅጥረኛነት ዘመናቸውን ለማራዘም ያዳክራሉ።

አስቀድሞ የወያኔውና የሻእቢያ መሪዎች እነአቶ መለሰ ዜናዊና አቶ ኢሳኢያስ አፈወርቂ ስልጣን ከመብቃታቸው በፊት ዋሽንግተን ተጠርተው ታማኝ ቅጠረኛነታቸውን አረጋግጠው መመለሳቸውም አይዘነጋም። ወያኔና ብጤዎቹ የሽግግር መንግሥት በአዲስ አበባ እንዲመሥርቱ በታዘዙት መሠረት አቋቋሙ።

ቀጥሎም የወያኔ የሽግግር መንግሥት ተብዬው የሥራ መመሪያ ወረቅት ( a policy frame work paper) ከዋሽንግተን ከተማ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) እና በዓለም ባንክ (World Bank) ተዘጋጅቶ እንዲያስፈጽም ተላከለት። በዓለም ባንክ የተለመደ መመሪያ ማለትም የመዋቅር ማስተካከያ መርሃ ግብር (Structural Adjustment Programme, SAP) መሠረት አያሌ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች ከየድርጅቱ በቅንሳ መልክ ተባረሩ። አስተማሪዎች፣ የጤና ባለሙያዎች እንኳ ሳይቀሩ ተቀነሱ። የወባ ማጥፊያ ተቋማት ተዘጉ። የዓለም ባንክ ፕሮግራም ለወያኔ የጎሳ ማጽዳት ዘመቻ መልካም አጋጣሚን ፈጠረለት። በኢኮኖሚ መዋቅር ማስተካከያ ለውጥ ሽፋን ብዙ ሺህ ወራተኞች ተባረው ለድህነት ሲዳረጉ የገቹው መደብ የወያኔና የሻእቢያ ካድሬዎች ግን በሁሉም የመንግሥት ድርጅቶች፣ ፋብሪካዎችና የአስተዳደር እርከኖች ከላይ እስከ ታች ድረስ በብዛት ተሰገሰጉበት።

የዓለም ባንክ የመዋቅር ማስተካከያ በኢትዮጵያ ርሃብንና ማኅበራዊ ቀውስን ይበልጥ አባብሶታል።

ለዚህም ተጨባጭ ማስረጃ ኦክስፋም የተባለው ግብረ ሰናይ ድርጅት ስለ ዓለም ባንክ የመዋቅር ማስተካከያ የገለጸውን ይመለከቷል፣

በመሆኑም ራስን በራስ መርዳትና ርሃብን ማስወገድ በምንም ዐይነት ተግባራዊ ሊሆን ከቶ አይቻልም።

ችጋር በመሠረቱ የማኅበርሰባዊ ፖለቲካ ቀውስ ውጤት እንጂ የእግዚአብሔር ቁጣና መቅሰፍትስ አይደለም። የችጋር መንስዔ የአካባቢ አየር ንብረት ለውጥ ብቻ ሳይሆን የሰዎች ድርጊት ክስተት ነው።
ለምሳሌ የአየርላንድ ችጋር (1845-1852) የድንች ሰብል መበላሸት ብቻ ሳይሆን የእንግሊዝ ቅኝገዥዎች በረሃቡ ወቅት በዚያ የነበረውን ሰብል ለውጭ ንግድ ይልኩት ስለነበር የብዙ ሚሊዩን አየርላንድ ሕዝብ በችጋር አለቀ። እ.አ.አ 1942 ዓም በሕንድ ከሁለት ሚሊዩን በላይ ሕንዳውያን በችጋር ያለቁት በሕንድ አገር ሩዝ በመጥፋቱ ስይሆን እንግሊዞች ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት ገንዘብ ማግኛ ሲሉ ለውጭ ንግድ ትርፍ በማዋለቸው ነበር።
በኢትዩጵያ ዘወትር ጥራጥሬዎች ለምሳሌ ሽንብራ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ምስር እንዲሁም የቅባት ሰብሎች ሰሊጥ፣ ስፍ፣ ኑግ፣ ጉሉ ወዘተረፈ እየተመረቱ ለዓለም ገበያ ቀርበው የውጪ ምንዛሪ ያስገኛሉ። በፕሮቲን ንጥረ ምግብ የበለፀገውን ጥራጥሬ ውጪ በመለካ ያልተመጣጠነ አመጋገብን አስከትሏል። የኢትዩጵያ የሥጋ ሃብት ለአረብና አውሮፓ ገበያ ሲውል የኢትዩጵያ ሕዝብ ግን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዳያገኝ ተደርጓል። ገበሬው በጥንታዊ መሥሪያ በከፍተኛ ድካም የሚያመርተውን ልዩ ልዩ ሰብል በርካሽ ዋጋ ሸጦ ዘወተር በድህነት ይኖራል። በአንፃሩ ግን እፍኝ የማይሞሉት መንግሥት ተብዬ የአቀባባይ ከበርቴዎች ጥርቃሞ የቅንጦት ኑሮ ዋናው ምንጭ ገበሬውን በመብዝበና የውጭ የምግብ ርድታ ጥገኛ በማስደረግ ነው።
የኢትዩጵያ ገበሬ ከአፍሪቃና ከዓለም ተለይቶ የድርብ ድርብርብ ግፍና በደል ተሽካሚ የሆነው
በአየር ንብረት መለዋወጥ የድርቅ ሰለባ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ወታደራዊ ደርግ ያለአግባብ በመላው አገር የወረሰው የገጠርና የከተማ መሬት ይዞታው ስሪት ነው። ገበሬው የመንግሥት ተብዬ ቅጥረኛ ጥርቃሞ ጭሰኛ ነው። የደንቆሮ ካድሬ መፈንጭያ አሸንጓሊት፣ ካባላባት የጭሰኛ ስርዓት እጅግ በጣም የከፋ ብዝበዛና ጭቆና ይደረግበታል። የራሱ የሆነ የግል የመሬት ይዞታ መብት እንደ ጎረቤታችን ኬኒያ፣ ጅቡቲና ሱዳን፤ እንደ ግብፅ፣ ናይጀሪያ፣ ሞረኮ፣ አሜሪካ፣ ካናድ፣ ጣሊያን፣ ጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ ግሪክ፣ ሕንድ፣ ብራዚል፣ ወዘተረፈ የለውም።
የግል ባለንብረትነት መብት ያለመኖሩና የይዞታው መጠን እጅግ በጣም አነስተኛነት በበቂ ለማምረት አላስቻሉትም። ኢትዩጵያ ለግብርና የሚሆን በጣም ለምና ስፋፊ ለመስኖ አገልግሎት የሚሆን ድንግል መሬት አላት። ይሁንና ይህን ለም መሬት ለአገሩ ሰው ለገበሬው በሥርዓት ሳይከፋፈል በነፃ ገበያ ሽፋን ለውጭ ትላልቅ የሕንድ፣ የአረብና፣ የአውሮፓ ኩባንያዎች በርካሽ ይሸጣል።
የወያኔ መንግሥት ገበሬዎችንና የአፋር አርብቶ አደሮችን በያለበት ከይዞታቸው በግዳጅ ያፈናቅላል። በደቡብ ክልል በማጅ

ሌላው ሃያ ከመቶው በላይ የሚሆነው የምግብ ርዳታ የሚከፋፈለው በጭራሽ ለማያስፈልጋቸው ገበሬዎች ሲሆን 30 ከመቶ ደግሞ ለቀጥታ ፍጆታ ሳይሆን ለአካባቢው ገበያ ሽያጭ ነው።
በዚህ ዓይነት ኢትዮጵያ ከአፍሪቃ በሕዝብ ብዛት ሦስተኛዋ አገር ለአሜሪካና አውሮፓ ለከፍተኛ የድጎማ ዘመናዊ ገበሬዎች ምርት ማራገፊያ ሆናለች።

## የዐይነቶች ዝርፊያ (Biopiracy)

የምግብ ርዳታ መርህ ርሃብን ለማባባስ እንጂ ለማስወገድስ ከቶ አይደለም። መቼም የዓለም ሕዝብ በጠቅላላው፣ ይልቁንም አፍሪቃውያን ስለኢትዮጵያ ችጋር ዝንተ ዓለም መስማት በጣም ያስምማቸዋል። የምግብ ርዳታና ችጋር ማስታገሻ የተባሉት የምዕራብ ባዮቴክ ኮርፖሬሽኖች የባሕላዊ የእዝርእት ዘሮችን ለግል ንብረትነት የሚዘርፉበትና የሚወርሱበት፣ ኢኮኖሚያዊ ሉላዊነት የሚያስፍኑበት፣ የዘር እንዱስትሪዎቻቸው ተጠናክረው የወጡበት በጣም ወራዳ ማጭበርበሪያዎች ናቸው።
የኢትዮጵያ ገበሬዎች በአፍሪቃ የአባይ ሸለቆ ለአያሌ ሺህ ዘመናት ያለመዷቸውንና ያራቡዋቸውን ጠቃሚ የሰብል ዘር ዓይነቶችን ባለንብረትነት መብት የምዕራብ ኩባንያዎች እንደ ሞንሳንቶ፣ ካርጊል፣ ዱፖንት፣ ክራፍት፣ ዩኒሊቨር ወዘተረፈ የመሳሰሉት ለመንጠቅ ተሰማርተዋል።
ለምሳሌ የጤፍን አሥር ዐይነት ዘር የወያኔ መንግሥት ለሆላንድ ኩባንያ (Soil and crop Improvement) ባለንብረትነት ሸጧል። ኩባንያው ዘሩን የራሱ ንብረት አድርጎ አውሮፓ ውስጥ ጤፍን በማምረት ግሉቲንየለሽ ኬኮች፣ ብስኩቶችና ዳቦ ለገበያ ያቀርባል።
የኢትዮጵያ ገበሬ የራሱን ዘር ትቶ ድቅልና መወራርሻ ልውጥ (GM seeds) ዘር በየጊዜው ከምዕራባውያኑ የዘር ኩባንያ እንዲገዛ ታስቦ ባሕላዊ የዘር ዓይነቶችን ከገጠር ሩቅ መንደር ድረስ ዘልቀው በመግባት ሰብስበውና አስብስበው ወስደዋል።
ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ጥንታዊት አገር ናት ስንል እንዲያው ራስን በከንቱ ለማኩራራት ሳይሆን በሥነ ፍጥረት ምርምር ግንዛቦት የሩሲያ የሥነ ሕይወት ሊቅ ቫቪሎቭ እንዳረጋገጡት ከዓለም ስምንቱ የመወራረሻ ምንጮች / genetic centres / አንዷ በመሆኗ ነው እንጂ።
ኢትዮጵያ ለዓለም ከአበረከታቻቸው የጠቃሚ ሰብል ዓይነቶች ለምሳሌ የስንዴ፣ የገብስ፣ የማሽላ፣ የሱፍ፣ የኑግ፣ የጤፍ፣ የአተር፣ የሽንብራ፣ የጉሎ፣ የቡና፣ ወዘተረፈ። ከኢትዮጵያ የተሰረቀው የገብስ ዘርያ ለአሜሪካንና ካናዳ ገበሬዎች የብዙ ሚሊዮን ያሜሪካ ብር ገቢ ሲይስገኝላቸው የኛ ገበሬ አንድም ሳንቲም አለማግኘቱን ዶክተር ሳዕከ ማርያም ደምሴ አስረድተዋል። (A vast historical

ነፃ ባልሆነው ነፃ ገበያ የግብርናው ግብአቶች ሁሉ በወያኔዎችና የባሕር ማዶ ሸሪኮቻቸው በሞኖፖል ተይዟል። የመንግሥት ጭሰኛ የሆኑት ገበሬዎች ያለ ፈቃዳቸው በግዳጅ ማዳበሪያ እንዲገዙም ይገደዳሉ።

ለምሳሌ የኖሮዌው የኬሚካል ማዳበሪያ ሺያጭ ድርጅት በኢትዮጵያ ገበያውን ለመቆጣጠር ሲል ለወያኔ ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ መለሰ ዜናዊን መርጦ መሸለሙ አይዘነጋም።

በልውጥ ዘሮች (GM seeds) ጥገኝነት ለችጋር መግባት በሩ ወለል ብሎ ተከፈቶለታል። ስለሆነም ለገበሬው ኢኮኖሚያው ውድቀትና ለአካባቢዊ የዐይነቶች ውድመትና ብክለት ማስከትሉ የተረጋገጠ ነው።

በኢትዮጵያ ያለው ነባራዊ ሁኔታ በሕንድ ከደረሰው ጋራ ይነፃፀራልና ቀጥሎ እንመልከተው።

ታዋቂዋ ያካባቢ ደህንነትና የዐይነቶች ዐቃቢና ተንከባካቢዋ ፕሮፌሰር ቫንዳና ሺቫ የርሃብ ችግር የፖለቲካው ዋና ዓላማ መሆን አለበት በሚል ርእስ ከጀርመን ድምፅ ጋራ እ.አአ 20.10.2008 ያደረጉትን ቃለ ምልልስ ያገናዝቧል። ( http:// www.dw-world.de/article / 0,2144,3717799,00.html)

በሕንድ የምግብ እጥረት አለ መንስዓውና መፍትሔውስ ምንድን ነው? ተብሎ ሲጠየቁ የሰጡት መልስ፣

<< ጦሱ በአረንጓዴው አብዮት ስም የተደረገው የተሳሳተ የግብርና ሞዴል ችግሩን ሳያስወግድ ይበልጥ አባብሶታል። በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ዐይነት ስብል (monoculture) ብቻ መዝራት ማለትም ስንዴና ሩዝ የማምረቱ ሂደት የሌሎችን ልዩ ልዩ ስብሎች ማምረት አሰናከለው። በሁለተኛ ደረጃ ከ1991 ዓ.ም ወዲህ የተጀመረው የመንግሥቱ ፖለቲካ መርህ ነው። ለንግዱን ክፍል በነፃ ገበያ እይታ ቅድሚያ ተሰጠ። የሕዝቡን መሠረታዊ የምግብ አቅርቦት በማረጋገጥ ፈንታ የግብርናው ምርት በመጀመሪያ ደረጃ ለውጭው ንግድ በእንዱስትሪ ለበለፀጉት አገሮች ገበያ አቅርቦት የበለጠ ትኩረት ስለሰጠ የመሠረታዊ ምግብ አቅርቦትን ጉዳይ ቸል አለው። ይህ ዓይነት ፖለቲካ የዓለም ባንክና የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) ዓላማ ተከትሎ የሚራመድ ነው። የመሠረታዊውን የምግብ ቁስቁስ ማምረት ፈጽሞ ተረስቷል። ፖለቲካውም በጭራሽ አይመለከትኝም ብሏል። ስለዚህም ዛሬ ሕንድ በዚህ በከሰረ የግብርና ፖለቲካ ትሰቃያለች። የአረንጓዴው አብዮት፣ የማወራረሻ ቴክኒክ / Genetic Engineering/ እንዲሁም **ነፃ ያልሆነ ነፃ ገበያና ንግድ ለርሃቡ ችግር ዋናው ምክንያት ናቸው።**

በመቀጠልም ባለፉት 10 ዓመታት ውስ ከ140ሺህ በላይ ገበሬዎች ራሳቸውን መግደላቸውና ስለምንስ ሁኔታው እንዲህ ተስፋቢስ ሊሆን ቻለ ተብለው ሲጠየቁ የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል።

እራስን መግደሉ የተጀመረው እ.አአ 1997 ዓ.ም አዲሱ የነፃ ገበያው የግብርናው ዘርፍ ፖለቲካ ያስከተለው ውጤት ነው። ኩባንያዎቹ እንደ ሞንሳንቶ ያሉት ወደ ገበያው ገብተው በጣም አጨናነቁት። ልውጥ ዘር፣ ኢታድሽ ድቅል ዘሮችን መሸጥ ጀመሩ። ይህ ዓይነቱ ዘር ደግሞ ብዙ ውሃ ያስፈልገዋል። ስለዚህ ገበሬዎች ለመስኖ ተግባር የሚያስፈልገውን መዋዕለ ንዋይ

የሚነሰነሰው ይህ ኬሚካል ማዳበሪያ በዝናብ ታጥቦ ወደ ወንዞችና ምንጭ ሲገባ የአካባቢውን የመጠጥ ውሃ ይመርዘዋል። በኢትዩጵያ አብዛኛው መሃይም ገበሬ ስለኬሚካል ማድበሪያ ምንም ዓይነት ዕውቀት የለውም። የማዳባሪያውን መጠንና ዓይነት ሳይታወቅ ፤ ከሰብሉ የቡቃያ እድገት ጀምሮ እስከ ማፍራት ከአሉት ሂደቶች ጋራ ተቀናጅቶ የማይደረግ ሳይሆን በግምት ብቻ መርጨት የዐፈሩን ዘላቂ ለምነትና ሥነ ምኅዳር ሊያቃውሰው እንደሚችል ግልጽ ነው። በአጠቃላይ በፍግና አረንጓዴ ማዳባሪያ ተጠቅሞ ለሥነ ምኅዳራዊ ተስማሚ ግብርናን አስቀይሮ የኬሚካል ማዳበሪያ ጥገኛና ማራገፊያ ለማሰደረግ ከፍተኛ ዘመቻ ይፈፀማል።

የኬሚካል ማዳበሪያ የዐፈሩን አሲዳማነት ሊጨምረው ይችላል።

በአሲዳማው ዐፈር ላይ የደቀቀ ኖራ ወይም ብክካ ብሃማ ዐፈር መርጨት ያፈሩን ለምነት እንደሚያሻሽለው ገበሬው ገና አያውቅም፤ እንዲያውቅም አልተደረገም፤ አይፈለግም። የምግብ ርዳታ ማራገፊያ ገበያ ሆኖ አንዲኖር ይፈለጋልና። በምግብ ለሥራ የሦስት ኪሎ ነቀዝ በላሽ ስንዴ ችሮታ ምርተቢስ ሥራ ጉልበቱን እንዲያባክንና ዘወትር ችጋር ገባ እየተባለ መለመኛ ሆኗል። በእዚህስ ሁኔታ እስከ መቼ?

ትግሉ ይቀጥላል!! አሉታ ኮንቱኑዋ!

የአፍሪቃ ቅጥረኛ ደላሎች ይውደማሉ! በሰሜን አፍሪቃ የተቀጣጠለው የነፃነት ፋና ያበራል!

ድል ለአፍሪቃ ገበሬዎችና አርብቶ አደሮች!

ድል ለኢትዩጵያ ሕዝብ!

ግራዋ ሳሙኤል
grawasamoyo@yahoo.co.uk